
# የ ሥላሴ (ሦስትነት) አስተምህሮ



## ለማስተማሪያ እና ለጥናት የተዘጋጀ

በዳዊት ፋሲል

1997/ጅማ

# የ"ሥላሴ"/ሦስትነት ትምህርት

- "ሥላሴ" የሚለው ቃል የግዕዝ ቃል ሲሆን በአማርኛ "ሦስትነት" የሚለውን ፍች ይሰጣል:: በእንግሊዘኛ ቋንቋ Trinity የሚለው ሲሆን ይህም Three-Unity ወይም "ሶስትነት"-በአንድነት የሚለውን የተሻለ ማብራሪያ ይሠጣል::
- ሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈጽሞ አይገኝም:: ይሁንና ሀሳቡን የሚገልጥ ትምህርት ግን እናገኛለን::
- በዓለም ላይ ከክርስትና እምነት በስተቀር በየትኛውም ኃይማኖት "ሦስት አካላት ያሉት አንድ አምላክ" የሚል አስተምህሮ አይገኝም:: ይህም ክርስትናን ከሌሎች እምነቶች የሚለየው ዋናው ትምህርት ነው::
- ቃሉ ሲብራራም "ሦስት አማልክት በአንድነት" ማለት ሳይሆን "አንድ አምላክ በሦስት አካላት" ማለት ነው::
- በሦስትነት የተገለጡት አካላት "አባት" "ልጁ" እና "ቅዱስ መንፈሱ" ናቸው ማቴ 28:19
- ሦስቱም አካላት እኩል መለኮታዊ ባህርያት አሏቸው:: ማለትም
- ሦስቱ አካላት - በዘለዓለማዊነት
    - በፈጣሪነት
    - ሁሉን በማወቅ (Omniscient)
    - በሁሉ ቦታ በመገኘት (Omnipresent) ወዘተ ፍፁም እኩልነት አላቸው::
- በመለኮታዊ ዕቅድ ሁሉ ውስጥ እያንዳንዱ አካል ተሳትፎ አለው:: እንዲሁም በአንዱ ዕቅድ ውስጥ እያንዳንዱ አካል የተለየ የራሱ የሆነ የሥራ ድርሻ አለው::

  በዚህ መሠረት: አባት(አብ) - ዕቅድ አውጪ (The Planner)
  ልጁ (ወልድ) - ዕቅዱ የሚፈጸምበት (Agent)
  ቅዱስ መንፈሱ - ዕቅዱ ወደ ተግባር እንዲመጣ ኃይል የሚያደርግ ነው:: (Revealer)

**ምሳሌ 1** አብ - ዓለማትን ሊፈጥር ወደደ
ልጁ - አባት በርሱ ዓለማትን ፈጠረበት
ቅዱስ መንፈስ - ሥራውን ያስፈጽም ነበር::
ዕብ 1:1-2, ቈላ 1:15-17, ዮሐ 1:3, ዘፍ 1:2

**ምሳሌ 2** አብ - ዓለምን ለማዳን ወደደ ልጁን ላከው
ልጁ - ዓለምን ለማዳን ሥጋ ለበሰ
ቅዱስ መንፈስ - ኢየሱስ ራሱን በዘላለም መንፈስ አቀረበ
ዮሐ 3:16, ዮሐ 1:14, ዕብ 10:5, ዕብ 9:14

## ጥቅሞች

- የሥላሴን ትምህርት በአግባቡ ማወቅ ብዙ ጥቅሞች ያሉት እና መሠረታዊው ጉዳይ ሲሆን ዋነኛ ጥቅሞቹ ግን የሚከተሉት ናቸው::
    1. የምናመልከውን እንድናውቀው ዮሐ 4:22
    2. ስለ ክርስቶስ ማንነት (Christology) እንድናውቅና ራስን ከተቃዋሚው መንፈስ ለመጠበቅ 1ዮሐ 4:1-4
    3. ስለመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ማንነት በመረዳት ከእርሱ ጋር ላለን ሕብረትና ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን ጥንቃቄ እንድናደርግ ይጠቅመናል::

## ታሪክ

- በመጀመሪያ አንድ አማኝ ልብ ሊለው የሚገባ ነገር ቢኖር «ሥላሴ» የሚለው ቃል የእግዚአብሔር መጠሪያ ስም አለመሆኑን ነው:: "**ሥላሴ**" የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚያስተምረው የትምህርት ርዕስ እንጂ መጠሪያ ስም አይደለም:: የቃሉ ትርጉም "**ሦስትነት**" ማለት እንደሆነ ልብ ይሏል::
- "**ሥላሴ**" የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት ሰው "**ተርቱሊያን**" /Tertulian/ /ከ160-220 ዓ.ም./ የተባለው የቤተክርስቲያን መሪ ነበር::
- ቱርቱሊያን በርሱ ዘመን ለተነሱትና በእግዚአብሔር የአንድነት ሶስትነት ጉዳይ ላይ ግራ ለገባቸውና ጥያቄ ላነሱ ሰዎች በተለይ ኘራግዚያስ/Praxeas/ - ለተባለው ሰው ክህደት ነገሮችን ለማስተማር እና የአምላክን በሦስት አካላት የተገለጠ አንድ አምላክነት ለማብራራት ሲል "በሦስትነት አንድነት" Tri-Unity የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቅሟል::
- የሥላሴ አስተምህሮ ወደመሠረታዊ ትምህርትነት እንዲያድግ ያደረገው ቤተክርስቲያን በተለያየ ጊዜ ባደረጋቻቸው ስብሰባዎች ያስተላለፈቻቸው የእምነት መግለጫና ውሳኔዎች ናቸው:: በወቅቱም ቤተክርስቲያን አጠቃላይ ስብሰባዎች እንድታደርግ ያነሳሷት 3 ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ነበሩ
    1. የአምላክ አንድነት እና በሦስት አካላት መገለጥ
    2. የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት
    3. የመንፈስ ቅዱስ አካልነት እና አምላክነት ጥያቄ ነበሩ::

- በእነዚህ ጉዳዮች ላይ እንድትወያይም ዋነኛ ምክንያት የሆኑት በዘመኑ ተነስተው የነበሩ የተለያዩ እንግዳ ትምህርቶች ነበሩ:: እነዚህም አስተምህሮዎች

**1ኛ. ሞናርኪያኒዝም (Monarchianism)**

**1.1 ራስን መለወጥ** (Modalistic Monarchianism)

ይህም አንድ አካል ያለው አምላክ ራሱን በመለዋወጥ እንደ ሦስት ሆኖ ሠራ እንጂ ሦስት አካላት የሉም የሚል ትምህርት

**1.2 በመክበር አምላክ መደረግ** (Adoptionistic monarchianism)

ኢየሱስ በራሱ አምላክ አይደለም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በጥምቀት ጊዜ ከፍ ከፍ አድርጎት፣ በማክበር አምላክ አደረገው የሚል ትምህርት

**2ኛ. አርዮሳውያን (Arianism)**

ኢየሱስ ፈጽሞ የባህሪይ አምላክ አይደለም የአብ ፍጥረት እንጂ ከአብ ጋር በመጀመሪያ አልነበረም የሚል ትምህርት

- ከላይ የተዘረዘሩት በወቅቱ እንግዳ የነበሩ ትምህርቶች እየተስፋፉ ሲመጡ ቤተክርስቲያን ደግሞ እውነተኛውን አስተምህሮ ለማስጠበቅ ስትል በ325 ዓ.ም. በኒቂያ ከተማ አጠቃላይ ጉባኤ በማድረግ "ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ ጋር እኩል የሆነ መለኮታዊ ባህሪይ አለው" በማለት ወሰነች፡፡
- እንዲሁም በ381 ዓ.ም. መንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆነ አካል ያለው መለኮት እና በመለኮታዊ ባህሪይ ከአብና ከልጁ ጋር እኩል እንደሆነ የሚያረጋግጥ ውሳኔ አስተላለፈች፡፡
- እንግዲህ ከእነዚህ ጊዜያት በኋላ የሥላሴ /ሦስት አካላት አንድ አምላክ/ ትምህርት በቤተክርስቲያን የተጠናከረ ትምህርት ተሰጥቶበታል፡፡

## <u>መንፈሳዊውን ነገር በመንፈስ መመርመር</u>

- የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚ የሆነ ደቀመዝሙር የሥላሴን ትምህርት በቀጥታ ዓረፍተነገር የሚገልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ባያገኝም ነገር ግን ይህንኑ አስተምህሮ የሚያብራሩ የተለያዩ ጥቅሶችን ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያገኛል፡፡
- ስለዚህ ደቀመዝሙሩ እግዚአብሔር የሰወራቸው ብዙ ምስጢሮች እንዳሉና (ዘዳ 29:29) እነዚህንም መረዳት የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ላይ በመደገፍ ብቻ እንደሆነ ሊያውቅ ያስፈልጋል፡፡ (1ቆሮ 2:13)
- ሰዎች አንድን ነገር ለማመን (ለመቀበል) የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ፡፡
  - Rationalism /ምክንያታዊነት/ - ተጨባጭ የሆኑ ማስረጃዎችን ወይም ምክንያቶችን በማግኘት ማመን
  - Empiricism (በመሞከር ማረጋገጥ) ለምሳሌ የስሜት ሕዋሳቶችን በመጠቀም በመዳሰስ፣ በመቅመስ ወዘተ ማረጋገጥ
  - Faith (እምነት) - የእግዚአብሔር ቃል ብቻውን መንፈሳዊ ነገሮችን ለመበየን ሥልጣን እንዳለው በማመን መቀበል፡፡ ተጨባጭ በሆኑ ምክንያቶችና፣ በሙከራ የማይደረስባቸውን መንፈሳዊ ነገሮች የምንረዳው በቃሉ ውስጥ የተፃፉትን ሁሉ ያለጥርጥር አምኖ በመቀበል ነው፡፡

## መለኰታዊ ባህርያት

- የሥላሴ አስተምህሮን (The Doctrine of the trinity) በአግባቡ ለመረዳት የመለኮታዊ ባህሪያትን (Divine Essence) ምንነት ማጥናት አስፈላጊ ይሆናል::
- መለኮታዊ ባህርያት የምንላቸው አምላክ ብቻ ሊኖሩት የሚችሉ እና የትኛውም ከአምላክነት ያነሰ ወይም ፍጹም አምላክ ያልሆነ ሊኖረው የማይችል ባህርያት ናቸው::
- እንግዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት የተለያዩ አካላት አባት፣ ልጁ፣ እና ቅዱስ መንፈሱ መኖራቸው ግልጽ ሲሆን እነዚህ አካላት ፍፁም መለኮት ለመሆን እነዚህን ባህርያት ሊያሟሉ ይገባቸዋል ማለት ነው::

1. **ሁሉን ማወቅ (Omniscience):-** ሁሉንም ነገር ማወቅ አምላክ ብቻ ሊኖረው የሚችል ባህርይ ሲሆን ሦስቱም አካላት ይህንን ባህርይ ያሟላሉ::

   አባት: 1ሳሙ 2:3, መዝ 139:1-5, ሮሜ 11:33

   ልጁ: ዮሐ 2:24,25 ሉቃ 6:8, ዮሐ 16:30

   ቅዱስ መንፈሱ: 1ቆሮ 2:10

2. **ሁሉን ማድረግ መቻል (Omnipotent)**

   አባት: ዘፍ 17:1, ኢዮ 42:2, ኤር 32:27

   ልጁ: ዮሐ 1:3, (መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ተአምራት በሙሉ)

   ቅዱስ መንፈሱ: ሉቃ 1:35,ዘካ 4:6

3. **በሁሉ ቦታ መገኘት (Omnipresence)**

   አባት: መዝ 139:7-11, አሞ 9:2-3, ኤር 23:23

   ልጁ: ማቴ 28:20, ቈላ 1:27, 2ቆሮ 3:17, ማቴ 18:20

   ቅዱስ መንፈሱ: መዝ (139):7

4. **ፈጣሪነት**

   አባት: ዘፍ 1:1, ኢሳ 40:28, ኢሳ 44:24

   ልጁ: ዮሐ 1:3, ቈላ 1:15-17, ዕብ 1:10

   ቅዱስ መንፈሱ: ዘፍ 1:2, ኢዮ 33:4, መዝ 104:30

5. **ዘላለማዊነት**

   አባት: ኢሳ 41:4, ኢሳ 44:6, መዝ 90:2

   ልጁ: ራዕ 1:17, ራዕ 22:13

   ቅዱስ መንፈሱ: ዕብ 9:14 (eternal Spirit)

**ማስታወሻ:-** የአምላክን ዘላለማዊነት ከፍጥረት ዘላለማዊነት የሚለየው አምላክ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም (የነበረና የሚኖር) ሲሆን ለእኛ የተሰጠን ዘላለማዊነት ግን ከተፈጠርንበት ቀን ጀምሮ ብቻ የሚኖረው የወደፊቱ ዘላለም ብቻ ነው::

## ሥላሴ በብሉይ ኪዳን

- እግዚአብሔር ሦስት አካላት ያሉት አንድ አምላክ ነው ካልን እርሱ በብሉይ ኪዳን ዘመንም ያው እርሱ ነውና ራሱን ከአንድ በላይ በሆነ አካላት ሲገልጥ ማግኘት ይኖርብናል።
- ብዙ ሰዎች ሥላሴ የአዲስ ኪዳን ትምህርትና መገለጥ ብቻ ይመስላቸዋል። አምላክ ግን በብሉይም ኪዳን ራሱ ከአንድ ወይም ከሁለት አካላት በላይ እንዳሉት በሚያሣይ መልኩ ተገልጧል።
- ይሁን እንጂ አምላክ እስራኤሎችን በዙሪያቸው ካሉት የአህዛብ የአምልኮ ልማድና ከብዙ አማልክት ራሳቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ የእሱን አንድ አምላክነት አጥብቆ ይነግራቸው ነበር። ዘዳ 6:4 ( አንድ አምላክ እንጂ አንድ አካል አይልም)።
- ይህም የሆነበት ምክንያት ከላይ እንደተጠቀሰው አህዛብ ጐረቤቶቻቸው ብዙ አማልክት አምላኪ (Polytheists) ስለነበሩ ነው። በአህዛብ እምነት ሁሉም ነገሮች ለምሳሌ ባህር፣ ሜዳ፣ ተራራ፣ ሰማይ፣ መብረቅ፣ ዝናብ ወዘተ ለእያንዳንዳቸው የየራሳቸው የሆነ አምላክ አላቸው ብለው ያስቡ ነበር። ከዚህም እምነት (henotheism) እስራኤል እንዲጠበቁ እግዚአብሔር ብቻውን የሁሉም ነገሮች አምላክ እንደሆነ ያሳስባቸው ነበር። ኢሳ 45:22, መዝ (96):5

## ሀ. በብሉይ ኪዳን የሚገኙ በርካታ ጥቅሶች እግዚአብሔር ከአንድ በላይ በሆነ አካላት መገለጡን ያሳያሉ።

1. **ዘፍጥረት 1:1 እግዚአብሔር (Elohim)**

   "እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ" የሚለው ምንባብ በዋናው የእብራይስጡ (Original) መጽሐፍ ላይ ኤሎሂም ሰማይንና ምድርን ፈጠረ በማለት ይገልጸዋል። በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥም እግዚአብሔር ተብሎ የተተረጐመው ስም በአብዛኛው ሙሴ "ኤሎሂም" ብሎ የፃፈው ነው። (አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ተመልከት)

   **ኤሎሂም** - የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ይህም ለብዙ ቁጥር የሚያገለግል ነው።

   **ኤል** - ኃያል አምላክ (ነጠላ ቁጥር)

   **ኤሎሂም** - ኃያላን አምላኮች (ብዙ ቁጥር) የሚለውን ስሜት ሲሰጥ ይህም በአንድ ማሠሪያ አንቀጽ ፈጠረ በሚል መዘጋቱ አንዱ አምላክ ከአንድ በላይ በሆነ አካላት እንደተገለጠ ያሳያል።

2. **ዘፍጥረት 1:26 እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር::**

   አለ - ***ነጠላ ቁጥር***

   በመልካችን እንደምሳሌያችን - ***ብዙ ቁጥር***

- አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር እንፍጠር ብሎ የተማከረው ከመላእክት ጋር ነው ይላሉ:: እግዚአብሔር ግን ከማንም ጋር አይመካከምር:: እንዲሁም መላእክት በመፍጠር ሥራ ተሳታፊ አይደሉም:: ራሳቸው ፍጡራን ናቸውና:: ኢሳ 40:13-14, ኢሳ 44:24, ኤፌ 1:11

3. **ዘፍጥረት 3:22 እግዚአብሔር አምላክም አለ ...አዳም ከእኛ እንደአንዱ ሆነ**

   አለ - ***ነጠላ ቁጥር***

   ከእኛ እንደአንዱ - ***ብዙ ቁጥር***

4. **ዘፍጥረት 11:7 እግዚአብሔርም አለ... ኑ እንውረድ ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው**

   አለ - ***ነጠላ ቁጥር***

   ኑ እንውረድ/እንደባልቀው - ***ብዙ ቁጥር***

❖ ከሁለት አካላት በላይ መሆኑን ያሳያል:: ሁለት አካላት ብቻ ቢሆኑ ና! እንውረድ እንጂ ኑ! እንውረድ አይልም ነበርና::

5. **ኢሳያስ 6:8**

   *ማንን እልካለሁ* - ***ነጠላ ቁጥር***

   *ማንስ ይሄድልናል* - ***ብዙ ቁጥር***

## ለ. ሌሎች ጥቅሶች ደግሞ በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ አምላክ ወይም ጌታ የተባሉ የተለያዩ አካላት መኖራቸውን ያሳያሉ

1. ***መዝሙር* (45):6**

   አምላክ ሆይ ዙፋንህ ለዘለዓለም ነው (አንድ አካል)

   እግዚአብሔር አምላክህ የደስታ ዘይት ቀባህ (ሌላ አካል)

   ይህም አንደኛው አካል እግዚአብሔር አብ ሌላውን የአምላክ አካል ጌታ ኢየሱስን በሥጋው ወራት እንደቀባው ያሳያል (**ዕብ 1:8**)

2. ***መዝሙር* (110):1 "ጌታ ጌታዬን ..."**

- ኢየሱስ አይሁድ እንደሚያስቡት እርሱ ሰው ብቻ (የዳዊት ልጅ) ብቻ ሳይሆን የዳዊት ጌታ፣ የአምላክ አንዱ አካል መሆኑን ለማስረዳት ጥቅሱን በማስረጃነት ተጠቅሞበታል **(ማቴ 22:41-46)**

3. **ኢሳያስ 48:12-16** - በጣም በሚደንቅና በሚገርም ሁኔታ ሶስቱ አካላት የተገለጡበት ጥቅስ ነው::

- *ፊተኛና ኋለኛው ነኝ* - ጌታ ኢየሱስ
- ጌታ እግዚአብሔር - እግዚአብሔር አብ
- *መንፈሱ* - *መንፈስ* ቅዱስ (ሙሉውን ቁጥር በጥንቃቄ አንብበው)

## ሐ. የእግዚአብሔር መልአክ/ THE ANGEL OF YAHWEH

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት በብሉይ ኪዳን ዘመን ውስጥ ራሱን በተለያየ መንገድ ለሰዎች ገልጧል:: ይህም መገለጥ በሥነ-መለኮት ቋንቋ "Theophany" የመለኮት መገለጥ ይባላል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው እግዚአብሔር አብን አንድ ስንኳ ያየው እንደሌለና ሊያየውም እንዳይቻለው ይናገራል:: **ዮሐ 1:17** አብን የሚገልጠው ግን ሌላኛው አካል ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ነው:: **ዮሐ 6:46, 14:9 ቈላ 1:15-17,** ዕብ 1:3

ኢየሱስ ክርስቶስ (እግዚአብሔር ወልድ) በአዲስ ኪዳን በሥጋ ከመገለጡ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳንም ውስጥ በተለያዩ ሁኔታዎች ለሰው ልጆች ይገለጥ ነበር:: ይህም እርሱ ሌላኛው የመለኮት አካል መሆኑን በግልጥ ያሳያል::

- ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከተገለጠባቸው (Theophany) መንገዶች አንዱ የእግዚአብሔር መልአክ በመሆን ነው::
- (መልእክተኛ) መልአክ መስሎ መገለጡ ግን በአምላክነት ባህሪይ እንጂ በመልአክ ባህሪይ አልነበረም:: ምክንያቱም ኢየሱስ አምላክ እንጂ መልአክ አይደለምና (**ዕብ 1:1-14**)
- <u>ትኩረት</u> የሚከተሉትን ጥቅሶች ስናጠና በመልአክ መልክ የተገለጠው መለኮታዊ አካል እንጂ መደበኛ መልአክ እንዳይደለ በሚያሳየው መለኮታዊ ባህርያት ማወቅ እንችላለን::

**የእግዚአብሔር መልአክ (The Angel of YaHWeH)**

1. ራሱን እግዚአብሔር ብሎ ይጠራል
2. የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ <u>አምላክ ነኝ</u> ይላል
3. ስግደት ይቀበላል መደበኛ መላዕክት ግን ስግደት አይቀበሉም (ራዕ **19:10**, 22:8)
4. መለኮታዊ የመባረክ ሥልጣን (እኔ) አለው
5. እግዚአብሔር ስለሆነ ለእግዚአብሔር ብቻ የተፈቀደውን መስዋዕት ይቀበላል ወዘተ ...

ከላይ በርዕሱ የተዘረዘሩት ባህርያት ደግሞ የመለኮት ብቻ ባህርያት ሲሆኑ ፍጡር ከቶውኑም እነዚህ ባህርያት ሊኖሩት አይችልም::

**ጥቅሶቹን ልብ ብለህ አጥና**

1. ዘፍጥረት 16:7-14 (መጀመሪያ አንብበው)
   - ሀ. ዘርሽን እጅግ አበዛዋለሁ (ቁ. 10)
   - ለ. ይናገራት የነበረውን የእግዚአብሔርን ሥም (ቁ. 13)
   - ሐ. ኤል - ሮኢ - እግዚአብሔርን አየሁት

2. ዘፍጥረት 22 (መጀመሪያ አንብበው)

   ሀ. እግዚአብሔርም ... ቁ. 1 እና ቁ. 11ን አነጻጽር

   ለ. የእግዚአብሔር መልአክ (ቁ. 11) አንድ ልጅህን <u>ለእኔ</u> አልከለከልክምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንህ (ቁ. 12)

   ሐ. ያህዌ - ይርኤ - እግዚአብሔር ያያል (ቁ. 14)

   መ. መለኮታዊ መባረክ (ቁ. 15-18)

3. ዘፍጥረት 31:11-13 (መጀመሪያ አንብብ)

   ሀ. የእግዚአብሔርም መልአክ በሕልም (ቁ. 11)

   ለ. የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ (ቁ. 13) ከዘፍ 28:12-22 ጋር አነጻጽር

4. ዘፍጥረት 32:22-30 (መጀመሪያ አንብበው)

   ሀ. አንድ ሰውም እስከ ንጋት ድረስ ቁ. 24

   ለ. ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ (ቁ. 28)

   ሐ. እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ (ቁ. 30)

   መ. ጵኒኤል - የእግዚአብሔር መገለጥ (ራዕይ) (ቁ. 30) (ሆሴዕ 12:4-6)

5. ዘጸአት 3:2-6 (መጀመሪያ አንብበው)

   ሀ. የእግዚአብሔርም መልአክ ... ታየው (ቁ. 2)

   ለ. እግዚአብሔር እርሱ (ሙሴ) ይመለከት ዘንድ እንደመጣ ባየ ጊዜ (ቁ. 4)

   ሐ. እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ (ቁ. 6)

   መ. ሙሴም እግዚአብሔርን ያይ ዘንድ ፈርቷልና (ቁ. 6)

   ሠ. እግዚአብሔርም አለ (ቁ. 7)

   ረ. ያለና የሚኖር (ጀሆቫህ ወይም ያህዌህ) እኔ ነኝ (ቁ. 14)

   ሰ. የዕብራውያን አምላክ ተገለጠልን (ቁ. 18)

6. ዘኍልቁ 22 (መጀመሪያ አንብበው)

   ሀ. ሲሰገድለት አልተቃወመም (ቁ. 31) ራዕ 19:10, 22:8

   ለ. ቁ. 35 እና ቁ. 38 አነጻጽር

   ሐ. ም. 22 35 እና ም 23:3-7 አነጻጽር

7. መሳፍንት 2:1-5 (መጀመሪያ አንብበው)

   ሀ. ከግብጽ አውጥቻችኋለሁ (ቁ. 1)

   ለ. ለአባቶቻችሁም ወደማልሁላቸው ምድር (ቁ. 1)

   ሐ. ከእናንተ ጋር ያደረግሁትን ቃልኪዳን (ቁ. 1)

8. መሳፍንት 6:11-25 (መጀመሪያ አንብበው)

ሀ. እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው (ቁ. 12)

ለ. እግዚአብሔርም ወደ እርሱ ዘወር ብሎ (ቁ. 14)

ሐ. እግዚአብሔር በእርግጥ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ... አለው (ቁ. 16)

መ. የምትናገረኝ አንተ እንደሆንህ (ቁ. 17)

ሠ. ቁርባን ይቀበላል (ቁ. 18) (ዘሌ 9:24)

ረ. እስራኤል የእግዚአብሔር መልአክ ማን እንደሆነ ግንዛቤ ነበራቸው ቁ. 22

9. መሳፍንት 13 (መጀመሪያ አንብበው)

ሀ. ማኑሄ ቁርባን ሳይሆን ግብዣ ለማድረግ ፈለገ (ቁ. 16)

ለ. የእግዚአብሔር መልአክ ግን ስለሚቃጠል መስዋት አመለከተው (ቁ. 16)

ሐ. ማኑሄ እግዚአብሔር እንደተገለጠለት ገና አላወቀም ነበር (ቁ 16)

መ. ስሜ ድንቅ ነው (ቁ.18) ከኢሳ. 9:6 ጋር አነፃፅር

ሠ. እግዚአብሔርን አይተናልና ሞት እንሞታለን (ቁ. 22)

ረ. የሚቃጠለውን መሥዋትና የእህሉን ቁርባን ከእጃችን ባልተቀበለን ነበር (ቁ.23)

**መስዋዕት የሚቀበል አምላክ ብቻ እንደሆነ ልብ በል።**

<u>ፍፁም የሆነ የሶስት አካላት መገለጥ በአዲስ ኪዳን</u>

- የጌታ ኢየሱስ የምድር አገልግሎት የሚጀምረው ግልፅ በሆነ የሶስት አካላት በአንድነት መገለጥ ነው።
- እንዲሁም በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በልዩ ልዩ ሥፍራዎች ላይ ሶስቱን አካላት የሚገልጡ ጥቅሶች እናገኛለን።

1. ማቴ 3:16-17 (አንብብ)
   - ልጅ (ወልድ) - በምድር ላይ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ይጠመቃል።
   - አባት (አብ) - በሰማይ ውስጥ የምወደው ልጄ ይህ ነው ሲል ይመሰክራል።
   - መንፈስ ቅዱስ - እንደ ርግብ ከሰማይ በልጁ ላይ ይመጣና ያርፋል።
2. ጌታ ኢየሱስ የምድር አገልግሎቱን ሲጨርስም ሥላሴን ያካተተ ትዕዛዝ አዘዛቸው **ማቴ 28:19**

   "በአብ፣ በወልድና፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው።" ከሶስቱ አካላት ያልተጠቀሱ፣ ወይም ያንሳል ተብሎ ያልተካተተ የለም። እንባቢው በዚህ የማጥመቂያ ስልጣን ባለው ስም ውስጥ የፍጥረት ስም ሊገባ ይችላል ብሎ ማሰብ እንዴት ይችላል?
3. 1ቆሮ 12:4-6
   - መንፈስ አንድ ነው (ራሱን የቻለ አንድ አካል)
   - ጌታም አንድ ነው (ራሱን የቻለ አንድ አካል)
   - እግዚአብሔርም አንድ ነው (ራሱን የቻለ አንድ አካል)

4. 2 ቆሮ 13:14
    - የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ (ወልድ)
    - የእግዚአብሔር ፍቅር (አብ)
    - የመንፈስ ቅዱስ ሕብረት (መንፈስ ቅዱስ)
5. ኤፌ 4:4-6
    - አንድ መንፈስ (አንድ አካል መንፈስ ቅዱስ)
    - አንድ ጌታ (አንድ አካል ወልድ)
    - አንድ አምላክ የሁሉም አባት (አንድ አካል አብ)
6. 1ጴጥ 1:1-2
    - እግዚአብሔር አብ
    - መንፈስ
    - ኢየሱስ ክርስቶስ (ወልድ)
7. ይሁዳ 20 - 21
    - በመንፈስ ቅዱስ እየፀለያችሁ
    - የኢየሱስ ክርስቶስ ምህረት (ወልድ)
    - በእግዚአብሔር ፍቅር (አብ)

## የሥላሴ ትምህርት ሶስት መሠረታዊ መግለጫ ነጥቦች

1. እግዚአብሔር ሶስት አካላት አሉት
2. እያንዳንዱ አካል ሙሉ የሆነ መለኮታዊ ባህርያት አሉት
3. እግዚአብአብሔር አንድ አምላክ ነው።

## 1. እግዚአብሔር ሦስት አካላት አሉት

እግዚአብሔር ሦስት አካላት አሉት ስንል አንዱ አካል ራሱን እየለዋወጠ በሶስት አካላት መልክ ይገለጣል ማለት አይደለም። ነገር ግን እያንዳንዱ ራሱን የቻለ ሶስት አካላት አሉት ማለት ነው። ይህም አብ ወልድ አይደለም ወልድ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ አይደለም ማለት ነው። ይልቁንም አብ ራሱን የቻለ አንድ አካል፣ ወልድም ሌላ አካል፣ መንፈስ ቅዱስም ሌላኛው አካል ማለት ነው።

**ጥቅስ**:- ዮሐ 1:1, ዮሐ 17:2, 1ዮሐ 2:1, ዕብ 7:25, ዮሐ 14:26

**2. እያንዳንዱ አካል ሙሉ የሆነ መለኮታዊ ባህርያት አሉት**

አስቀድመን እንዳጠናነው መለኮታዊ ባህርያት ስንል ፍፁም አምላክ ከሆነ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ፍጥረት ሊኖረው ወይም ከአምላክ ጋር ሊጋራው የማይችል ብቸኛ ባህርያት ማለት ናቸው:: ከአምላክ ያነሰ ወይም ፍጡር እነዚህ ባህርያት ሊኖሩት አይችሉም:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳችንን በጥንቃቄ ስናጠና እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዳቸው እነዚህ ፍፁም መለኮታዊ ባህርያት አሟልተው እናገኛለን::

**ጥቅስ:-** ዘፍ 1:1, ዮሐ 1:3, ኢዮ 33:4, ዘካ 14:3-5, 1ተሰ 3:11-13, ኢሳ 44:6, *ራዕ 1:17, ሐዋ 5:3,4, ሮሜ 8:11, ሐዋ 2:24, 32, 1ቆሮ 2:10-11 ወዘተ...*

**3. እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው::**

በሦስት አካላት የተገለፀው እግዚአብሔር በሰብአዊ ስሌት የሚሰላ ማንነት የለውም:: ስለሆነም አንድ አይነት መለኮታዊ ባህርያት ያሉት፣ የማይነጣጠል መለኮታዊ ሥልጣን ያለው አንድ አምላክ ነው:: እግዚአብሔር አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት ፈጽሞ አይደለም::

**ጥቅስ:-** ዘዳ 6:4, ማር 12:29, ያዕ 2:19, ዮሐ 10:30, ዮሐ 5:44, ይሁ 25, 1ቆሮ 8:4-6, 1ጢሞ 2:5

## የጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን የእምነት መግለጫ

**የሐዋርያት የእምነት መግለጫ (The Apostles creed)**
**(3ኛና 4ኛ መቶ ክ.ዘ.)**

"ሰማይንና ምድርን በሠራ፣ ሁሉን ማድረግ በሚችል በእግዚአብሔር አብ (አባት) አምናለሁ"
"አንድያ ልጁ በሚሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስም አምናለሁ፣ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣ በፖንቲየሱ ጲላጦስ መከራን በተቀበለ፣ በተሰቀለ፣ በሞተ፣ በተቀበረ፣ በሶስተኛ ቀን ከሙታን በተነሳው፣ ወደሰማይ ባረገው፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ(አባት) ቀኝ በተቀመጠው፣ በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ዳግመኛ በሚመጣው::"

"በመንፈስ ቅዱስም አምናለሁ" በአንዲት ቅድስት ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን በቅዱሳን አንድነት "በኃጢአት ይቅርታ፣ በሙታን ትንሣኤ፣ እና በዘላለም ሕይወት አምናለሁ"

-አሜን-

ይህ በጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን አማኞች ሁሉ ዘንድ ይታወቅ የነበረ የእምነት መግለጫ ነው:: በኋላም በኒሲያ አገር (325 ዓ.ም.) እና በኮንስታንቲኖኘል አገር (በ381 ዓ.ም.) ይኸው የእምነት መግለጫ በተብራራ መልኩ የቤተክርስቲያን የእምነት መግለጫ እንዲሆን ተወስኗል::

"አንባቢ ሆይ ከላይ የተዘረዘረውን የእምነት መግለጫ ከልብህ የምታምን ከሆነ አንተ ከጥንታዊቱ ቤተክርስቲያን አባላት አንዱ ነህ ማለት ነው::"

"This is a subject on which we know nothing except what is revealed"

Christian Catechism

# ዋቤ መጻሕፍት

## (References)


1. ቄስ ኮሊን ማንሰል (1995) "ትምህርተ እግዚአብሔር" አ.አ
2. ቄስ ኮሊን ማንሰል (1998) "ትምህርተ ክርስቶስ" አ.አ
3. ቄስ ኮሊን ማንሰል (1999) "ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ" አ.አ
4. Macled. D (2005), Shared Life – The trinity and the fellowship of God's people.
5. Grudem W. (1999) "Bible doctrine" Michigan.
6. Lawson R. (2003) "Christian Catechism, London.


**ከአዘጋጁ፡-** "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከአንተ/ከአንቺ ጋር ይሁን"

አሜን


☞ ***ዳዊት ፋሲል***

**ስ.ቁ. 0917804407**

**ፖ.ሣ.ቁ. 67 ጅማ**

E-mail – niguye2004@yahoo.com